# በራሪ ወረቀት - በቦታው ላይ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የሚጣል መመሪያ

## በቦታው ላይ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የሚጣል መመሪያ ምን ያደርጋል?

አንዳንድ ሰዎች እንደ ርእሰ መምህራን እና የትምህርት እና ስልጠና መምሪያ ሰራተኞች 'የተፈቀደላቸው ሰዎች' ይባላሉ። ወደ ትምህርት ቤቱ ሲሄዱ ወይም ከትምህርት ቤቱ ጋር ማንኛውንም ግንኙነት ሲፈጽሙ ሊከተሉዋቸው የሚገቡ መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን አላቸው።

መመሪያው ወደ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ወደሚደረጉባቸው ሌሎች ቦታዎች እንዳይገቡ ወይንም እዛ ቦታ እንዳይቆዮ ሊያግዱዎት ይችላል። መመሪያው ተግባራዊ የማይሆንባቸውን እንደ ጊዜ ወይም ቦታዎች ያሉ ዝርዝሮችን ሊያካትት ይችላል።

የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ስለሚጣሉ መመሪያዎች ተጨማሪ መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ። የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ስለሚጣሉ መመሪያዎች ለመረዳት እንዲያግዝዎት ቪዲዮውን እዚህ መመልከት ይችላሉ።

## በቦታው ላይ የሚጣል መመሪያ ለምን ያህል ጊዜ ተፈጻሚ ይሆናል?

እነዚህ ደንቦች ለምን ያህል ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆኑ መመሪያው በተጨማሪ ይገልጽልዎታል። መመሪያው ከ14 ቀናት በላይ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም።

## በትምህርት ቤቱ ውስጥ ልጅ ካለኝ፣ በቦታው ላይ የሚጣል መመሪያን መከተል ስላለብኝ ልጀ ላይ ምን ይደርስበታል?

ትምህርት ቤትዎ መመሪያው በልጅዎ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ተጽእኖ እና እርስዎ ልጅዎን እንዴት ሊንከባከቡ እንደሚችሉ በጥንቃቄ አስበበታል። መመሪያው እርስዎ ልጅዎን ከመንከባከብ ወይም ከትምህርታቸው ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ከመሳተፍ ለማገድ የታቀደ አይደለም።

ትምህርት ቤትዎ መመሪያውን ከሰጠዎት በኋላ በተቻለ ፍጥነት 'የመገናኛ እና የመዳረሻ ፕሮቶኮል' ይሰጥዎታል። ይህም የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካትታል።

- ስለ ልጅዎ ትምህርት መረጃ እንዴት እንደሚደርስዎት
- ልጅዎ እንዴት ወደ ትምህርት ቤት መሄዱን እንደሚቀጥል እና ልጅዎ በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ በመልካም ሁኔታ እንዴት መሳተፍ እንደሚችል ይዘረዝራል
- ልጅዎ ተገቢውን ድጋፍ እና እንክብካቤ ማግኘቱን ለማረጋገጥ ምን እንደሚያደርጉ።

## በቦታው ላይ በተጣለው መመሪያ የማልስማማ ከሆነስ?

መመሪያውን የጣለብዎ ስልጣን ያለው ሰው 'ቀጣይነት ያለው የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችል መመሪያ' ለመጣል ወይም የተጣለብዎን መመሪያ ለመሰረዝ መመሪያውን ከጣሉብዎ በኋላ ወዲያውኑ ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ቀጣይነት ያላቸው መመሪያዎችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ እዚህ በትምህርት እና ስልጠና መምሪያው ድረ ገጽ ላይ ይገኛል።

የተቃውሞ ደብዳቤው ውስጥ በጊዜው ለምን በዚህ መንገድ ያሳዮትን ባህሪ እንዳሳዮ አብራርተው፣ መመሪያው እርስዎን ወይም ልጅዎን በምን መልኩ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድርባቹህ ወይም ሌላ ማወቅ የሚያስፈልጋቸውን ነገር አካትተው በማንኛውም ጊዜ ማስገባት ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ልጅዎ አካል ጉዳተኛ መሆኑን ለትምህርት ቤቱ ነግረው ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ መደገፍዎን መቀጠል እንዲችሉ እና ይህንን እንዲደግፉ ሊያደርጓቸው ይችላሉ።

የተቃውሞ ደብደቤውን ወደ ተፈቀደለት ሰው በኢሜል ወይም በደብዳቤ ሊልኩት ይችላል። በትምህርት እና ስልጠና መምሪያው ድረ ገጽ ላይ የሚገኘውን አብነት ( template) መጠቀም ከፈለጉ እዚህ ማግኘት ይችላሉ።

ተቃውሞዎን በጽሁፍ ማቅረብ ካልፈለጉ፣ በምትኩ ተቃውሞዎን በቃል እንዲሰጡ መጠየቅ ይችላሉ። እርስዎን ወክሎ ሌላ ሰው ተቃውሞዎን እንዲያቀርብልዎ መጠየቅ ይችላሉ። ለምሳሌ የእርስዎ የአካል ጉዳት ድጋፍ ሰጭ ሰራተኛ ወይም አስተርጓሚ ሊሆን ይችላል።

## መመሪያውን ካልተከተልኩ ምን ይደርስብኛል?

በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን ደንቦች ካልተከተሉ፣ መመሪያውን እንዲከተሉ ለማስገደድ ትምህርት ቤቱ ጉዳዮን ወደ ፍርድ ቤት ሊወስደው ይችላል።

ፍርድ ቤቱ መመሪያን ባለመከተል ስህተት እንደፈጸሙ ካረጋገጠ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- የገንዘብ ቅጣት ሊጥልብዎ ይችላል
- መመሪያውን እንዲያከብሩ ሊያዝዎት ይችላል
- መመሪያውን ለማክበር የተለየ እርምጃ እንዲወስዱ ሊያዝዎት ይችላል
- ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም ነገር እንዲያደርጉ ሊያዝዎት ይችላል።

መመሪያውን ባለመከተልዎ አይታሰሩም፣ የወንጀል ሪከርድ አይመዘገብብዎትም ወይም የወንጀል ቅጣት አይጣልብዎትም።

## አስተርጓሚ (በቃል እና በጽሁፍ) ወይም ሌላ ድጋፍ ሰጭ አካል/ሰው ከፈለኩስ?

አስተርጓሚ (በቃል እና በጽሁፍ) ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰው ከፈለጉ፣ ይህንን ለትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ቢነግሩት(ሯት) ተገቢውን ድጋፍ እንዲያገኙ ሊረዱዎት ይችላሉ።

ልጅዎ የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ የሚማር (የምትማር) ከሆነ፣ የትምህርት እና ስልጠና መምሪያውን ክልላዊ ቢሮን በማነጋገር ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| ሰሜን ምስራቅ ቪክቶሪያ (North Eastern Victoria)<br>ስልክ: 1300 333 231<br>ኢሜይል: nevr@education.vic.gov.au | ሰሜን ምዕራብ ቪክቶሪያ (North Western Victoria)<br>ስልክ: 1300 338 691<br>ኢሜይል: nwvr@education.vic.gov.au |
| ደቡብ ምስራቅ ቪክቶሪያ (South Eastern Victoria)<br>ስልክ: 1300 338 738<br>ኢሜይል: sevr@education.vic.gov.au | ደቡብ ምዕራብ ቪክቶሪያ (South Western Victoria)<br>ስልክ: 1300 333 232<br>ኢሜይል: swvr@education.vic.gov.au |

## ተጨማሪ መረጃ ብፈልግስ?

የበለጠ መረጃ ለማግኘት የትምህርት እና ስልጠና መምሪያውን ድረ ገጽ እዚህ መጎብኘት ይችላሉ።